# የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ መልክዕ በአማርኛ

1 [1] በስመ እግዚአብሔር፡- የአምልኮት
ፍቅሩ ሐቅለ ኀሊና በሚያቃጥል
በእሳታዊ እግዚአብሔር ስም እና ይኽን
ከንቱ ሰነፍ ዓለም በአማላጅነት ድንቅ
ጥበቡ በምትፈውስ በኹለት ወገን
ድንግል በምትኾን አምላክን በወለደች
በድንግል ማርያም ስም ጽልመተ አበሳን
የምታስወግድ የብርሃን መቅረዝ ቅዱስ
ዮሐንስ ሆይ! ቸርነትህን እመሰክር
ዘንድ አዋጅ ነጋሪ ቅዱስ አንደበትህ
በአየረ ሰማይ በልዕልና ጐልቶ ይሰማ።

[2] ለጽንሰትከ፡- ያለ ኀጢአትና ያለ
ርኵሰት በቅድስና ሕግ ለተፈጸመ
ጽንሰትህ እና በወርኀ ሰኔ በሠላሳኛው
ዕለት ለሚከበር ልደትህ ሰላምታ
ይገባል፤ የሰማይ ደመናን ታዝዝ ዘንድ
ሥልጣን የተሰጠህ መጥምቀ መለኮት

# መልክዐ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በአማርኛ

**1** 1 **ለዝክረ ስምከ፡-** ያለ ፍጹም
መጉደል ጸጋና ሞገስን ለተመላ ስም
አጠራር ሰላምታ ይገባል፤ **ቅዱስ
ዮሐንስ** ሆይ! ሥጋዊ ደማዊ ስትሆን
መልአክ ነህ፤ የራእይህን ትርጓሜና
ሕጉን ዐውቅና እረዳ ዘንድ የጥበብን
ምንጭ እንደ ተከዜ ወንዝ ሙላኝ።

2 **ለሥዕርተ ርእስከ፡-** ቅብዐ ክህነትን
እንደተቀባ እንደ **አሮን** የሚጣፍጥ ሽቶ
የአርያም ጠል ለሆነው ለራስ ጠጕርህ
ሰላምታ ይገባል፤ ምድራዊ ስትሆን
ሰማይን የምትገዛው **ቅዱስ ዮሐንስ**
ሆይ! በአጠገቡ ወደተቀመጥህ ወደ
መምህርህ የእኔን የባሪያህን ድኅነት
ማልድ፤ የዓለምን ይቅርታ ማልድ።

3 **ለርእስከ፡- የእግዚአብሔር በግ**
የተባለ **የእግዚአብሔር ወልድ** መንበር

# መልክዐ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በአማርኛ

1 [1] ለዝክረ ስምከ፡- ያለ ፍጹም መጉደል ጸጋና ሞገስን ለተመላ ስም አጠራር ሰላምታ ይገባል፤ ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! ሥጋዊ ደማዊ ስትሆን መልአክ ነህ፤ የራእይህን ትርጓሜና ሕጉን ዐውቅና እረዳ ዘንድ የጥበብን ምንጭ እንደ ተከዜ ወንዝ ሙላኝ።

[2] ለሥዕርተ ርእስከ፡- ቅብዐ ክህነትን እንደተቀባ እንደ አሮን የሚጣፍጥ ሽቶ የአርያም ጠል ለሆነው ለራስ ጠጕርህ ሰላምታ ይገባል፤ ምድራዊ ስትሆን ሰማይን የምትገዛው ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! በአጠገቡ ወደተቀመጥህ ወደ መምህርህ የእኔን የባሪያህን ድኅነት ማልድ፤ የዓለምን ይቅርታ ማልድ።

[3] ለርእስከ፡- የእግዚአብሔር በግ የተባለ የእግዚአብሔር ወልድ መንበር በላዩ ላይ ለተሠራ ራስህ ሰላምታ ይገባል፤ በገጽታህ ንስር የተባልህ ኪሩብ ዮሐንስ ሆይ! በሰማያውያንና በምድራውያን በረከት መምህር ደግ ነህና ባርከኝ።

[4] ለገጽከ፡- በአምላክ በክርስቶስ ስቅለት ጊዜ የደም ግባቱ ልምላሜ ለጠወለገ ፊትህ ሰላምታ ይገባል፤ መልአክ ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! በጠዋትና በማታ እኔ አንተን እተማመናለሁ፤ በኀጢአት የሻከርሁ እኔን የአድነኝ (የአለሰልሰኝ) ዘንድ የተመሰገነ የፊትህ ደም ግባት በፊቴ ላይ ይፍሰስ።

5 **ለቀራንብቲከ፡-** የርግብ ዐይኖችህን ለሚሸፍኑ ለአንዱና ለሁለቱ ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል፤ ክርስቶስ የሚወድህ ደቀ መዝሙር ዮሐንስ ሆይ! የጨለማ ገዢ የሆነ ነፍሳትን የሚያድን (የሚያጠምድ) ጋኔንን ቅንድቦቼ ያሸንፉ ዘንድ በቅንድቦችህ ተማጽኛለሁ።

6 **ለአዕይንቲከ፡-** በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል መምህርህ ክርስቶስን ለተመለከቱ ዐይኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ ነባቤ መለኮት የክህነትና የመንግሥት ግንድና ቅርንጫፍ ዮሐንስ ሆይ! ከምሥራቅ ምዕራብ እንዲርቅ እንዲሁ የአንተ ጽድቅ የእኔን ኀጢአት ያርቅ።

7 **ለአእዛኒከ፡-** ሰባቱን የነጐድጓድ ነገሮች (ሰባቱን አጽርሐ መስቀል) የአዳምጡ ዘንድ ለነቁ ጆሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ ከመላእክት ጋር ስምም የሆንህ ዮሐንስ ሆይ! ጠላቱን እንደአሸነፈ ሰው ከንጽሕና ሳጥንህ የብርሃን መጽሐፍ እና የተሸሸገ መናን ስጠኝ።

8 **ለመላትሒከ፡-** ስለ ክርስቶስ ጽፋት (መመታት) በሐና እና በቀያፋ አደባባይ በመመታት (በመከራ) ለተገዙ ጉንጮችህ ሰላምታ ይገባል፤ በእሳት ማንደጃ ቤት ለሮምና የተገዛህ ዮሐንስ ሆይ! የአንተ ጸሎት ደመናን ተሻገረች የሚል ዜና በልቤ ውስጥ አሥርጽ (አብቅል)።

9 **ለአእናፌከ፡-** ጣፋጭ የሆነ የአርያም ዕጣንን ለአሸተቱ የሥጋ መስኮቶች ለሆኑ አፍንጫዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ በጥበብ ጐዳናዎች የሔድህ **ዮሐንስ** ሆይ! ከታሠረበት እንደሚፈታ ጥጃ እኔንም ከኀጢአት ማሠሪያ ፍታኝ፤ ለአንተም ምርኮ አድርገኝ።

10 **ለከናፍሪከ፡-** ባለሚልነት እንደ ውኃ ምንጭ ለሚፈሳቸው ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ **በጌታ ክርስቶስ** መሳም በቀለም እንደተነከረ ግምጃ ተነክረዋል (ተባርከዋልና)፤ **አቡቀለምሲስ** የተባልህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ከተመሰገነው መሥዋዕትህ ከንፈሬን ታስነካኝ ዘንድ ና፤ በከንፈሮቼ አበሳና እርክስና በዝቷልና።

11 **ለአፉከ፡-** ዋዕዩ (ግለቱ) ሳያቃጥለው የመለኮት አፍ ለሳመው አፍህ ሰላምታ ይገባል፤ ፍጥሞ በምትባል ደሴት ምሥጢርን የአየህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! የራእይህን ትርጓሜ ማንበብ መተርጐም እችል ዘንድ የአንደበትህን ማኅተም በእኔ ላይ ፍታልኝ (ግለጥልኝ)።

12 **ለአስናኒከ፡-** የአባቶችን ትራፊ ለአልበሉ (ለአላኘኩ) እንደ ወተት ነጫጭ ለሆኑ ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል፤ የተላከ ሐዋርያ እና ነቢይ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ንግግሬ የጣፈጠና የአማረ ይሆን ዘንድ ጨው ንግግርህ አልጫው አንደበቴን ያጣፍጠው።

13 **ለልሳንከ፡-** ሁለት መንገዶችን
ለሚናገር አንደበትህ ሰላምታ ይገባል፤
እነዚህም አንዲቷ የሕይወት አንዲቷ
የሞት ናቸው፤ የዕውቀትን ባሕር
የምትዋኝ የቋንቋዎች አባት **ቅዱስ**
**ዮሐንስ** ሆይ! ከእነዚህ ከሁለቱ መንገድ
ሕይወት በተሰኘችው ውሰደኝ፤ ከአንተ
ዘንድ የምመኛት ይኽች ናትና።

14 **ለቃልከ፡-** የተመሰገነ ወንጌልን
ከአስተማሩ ከሦስቱ ወንጌላውያን ይልቅ
ነገሩ ልዑል (ከፍ) ለአለ ቃልህ ሰላምታ
ይገባል፤ **የእግዚአብሔር** ወዳጅ ብፁዕ
**ዮሐንስ** ሆይ! በቃልህ ትእዛዝ ከእኔ ላይ
ክፉ የመከራ ጠላቶቼን ትበትንልኝ
ዘንድ ልመናየን በፊትህ አደርሳለሁ።

15 **ለእስትንፋስከ፡-** ሕይወትን
ለሚተነፍስ እስትንፋስህ ሰላምታ
ይገባል፤ ዳግመኛም የክህነትን ሥልጣን
ለሚሰጥ የእስትንፋስህ በረከት ሰላምታ
ይገባል፤ የጥበባት ባሕር **መምህር**
**ዮሐንስ** ሆይ! በሁለተኛ ልደት
የተቀበልሁትን የቀድሞ በንፍሐት
የአገኘሁት ጸጋየን በተመሰገነ
እስትንፋስህ አድሰው።

16 **ለጉርዔከ፡-** ከመዓር ከሰኮር ይልቅ
አነጋገሩ ለሚጣፍጥ የትንቢት ምንጭ
ለሆነ ጉሮሮህ ሰላምታ ይገባል፤ አባትህ
ዘብዴዎስን ከእነመረቡ ጥለህ የተከተልህ
**ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ሕገ ወንጌልን
ለወገኖቹ የምታስተምር **የእግዚአብሔር**
በሥጋ የቅርብ ዘመዱ ነህ።

17 **ለክሣድከ፡-** እንደ አማረ ጸንቶ ይኖር ዘንድ **እግዚአብሔር** ለመረጠው አንገትህ ሰላምታ ይገባል፤ የጥበብ ጌታ **የኢየሱስ** ባለሟል የወንጌል ሰባኪ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! **አምላክህ በመስቀል** ላይ ‹እነኋት እናትህ› እንደአለህ በመንግሥተ ሰማይ እናትህ **ማርያም** ከአንተ ጋር ናት።

18 **ለመትከፍትከ፡-** ከሰማይ ዙፋኑ ሳይጐድል **የልዑል እግዚአብሔር** መቀመጫ ለሆነ ትከሻህ ሰላምታ ይገባል፤ የጽዮን የደጇ ጌጥ ዕንቈ **ዮሐንስ** ሆይ! ከሚከብድ ድንጋይ ከሚጨንቅ ከአሸዋ ሸክም እጅግ የበረታ የኀጢአት ሸክም አመጻን ከትከሻየ ላይ አንሥተህ ጣልልኝ።

19 **ለዘባንከ፡-** ክንፉቸው ስድስት ከሆነ **ከሱራፌል** ክንፉቸው አራት ከሆነ **ከኪሩቤል** ለማያንስ ጀርባህ ሰላምታ ይገባል፤ ለተመሰገነ ለያዕቆብ ልጅ ለይሁዳ ለሆዱ ዕንቈ **ዮሐንስ** ሆይ! የሄኖክ ሰውነት የተሸሸገችበት (የተሰወረችበት) በአንተ ትመላለስ ዘንድ ነፍሴን የበቃች አድርጋት።

20 **ለእንግድዓከ፡-** የምስጋና ልብስ በማኅተም ቅርጽ በላዩ ላይ ለተዋሐደ (ለተቀረጸ) ደረትህ ሰላምታ ይገባል፤ የዓለም ሁሉ አገልግሎት በላዩ ላይ አለ፤ ከበረከትህ ዛሬ ትሰጠኝ ዘንድ በገዳም መስቀል ጽናት **ዮሐንስ** ሆይ! አማልኩህ።

21 **ለሕፅንከ፡-** ከጸጋ የተራቆተችበት ጊዜ ለሌለ የነበልባል መለኮት መጠጊያ ለሆነች ጭንህ ሰላምታ ይገባል፤ ለልጆቿ እና ለእመቤቲቷ መልእክትን የምትጽፍ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ፍጹም መከራ በሚጸናባት ዕለተ **ክርስቶስ** በተባለች በዕለተ ምጽአት የእኔ ማረፊያ ከአንተ ጉን ይሁን።

22 **ለአእዳዊከ፡-** የአይሁድ መምህር **ቅዱስ ጳውሎስ** የሰላም ምሶሶዎች እንዳለ የሰላም ምሶሶዎች ለሆኑ እጆችህ ሰላምታ ይገባል፤ የነጐድጓድ ልጅ መብረቅ **ዮሐንስ** ሆይ! የነፍስን መርከብ ሞገድ እንዳያውክ ከባድ ከሆነ ከበደል ማዕበል በእጆችህ ወልውለኝ (አንጻኝ)።

23 **ለመዛርዒከ፡-** በፍቅረ ቢጽ እና በፍቅረ **እግዚአብሔር** ‹በእነዚህ ሁለቱ ኦሪትና ነቢያት ጸንተው ይኖራሉ› ብለህ የአስተማርህ የገሊላው **ዮሐንስ** ሆይ! ለተመሰገነ ክንድህ ሰላምታ ይገባል፤ ለየዋህ በግ ከተኵላ ታድነኝ ዘንድ እኔ በጸሎት በተዘረጋ ክንድ እማጸናለሁ።

24 **ለኵርናዕከ፡-** በምስጋና አደባባይ ለሚቆሙ የስልሳ ኃይለኞች ኃይል ለአለው ኵርናህ ሰላምታ ይገባል፤ እንደ አንበሳ ልብህ የተማመነ ጽኑዕ **ዮሐንስ** ሆይ! በመረብ አስግረው ዓሣን እንደሚያወጡ በደል ከሞላበት ከዓለም ባሕር እኔን አውጣኝ።

25 **ለእመትከ፡-** ዐሥር ሺህ በመልአኩ
ክንድ የሆነውን እንደ አንድ ክንድ
አድርጐ ለከነዳ ክንድህ ሰላምታ
ይገባል፤ የሰማይ በር ተከፍቶ
የተመለከትህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ!
ለጠላቶቼ መዘባበቻ እንዳልሆን የአንተ
ክንድ የምትደግፍ እኅት ትሁነኝ።

26 **ለእራኅከ፡- እግዚአብሔር ወልድን**
በሥጋዌው ወራት ለዳሰሰ መሐል እጅህ
ሰላምታ ይገባል፤ **የእግዚአብሔር** ጸጋ
የተሠጠህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ከመሐል
እጅህ በታች ራሴን አደርጋለሁ፤
ከብርና ከወርቅ ይልቅ የአንተን መሐል
እጅ እመርጣለሁ።

27 **ለአፃብዒከ፡-** የምትወደው የጋይዮስን
ሥራዎች ለጻፉ ጣቶችህ ሰላምታ
ይገባል፤ ለማስተማርና ለመስበክ
የተላክህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ!
በተንኮልና በክፋት ክብሩን ጥሎ
ከተዋረደ ከዲያብሎስ በጸሎትህ
ጠብቀኝ።

28 **ለአጽፋረ እዴከ፡-** ከዐሥሩ ጣቶችህ
ጋር ለተስማሙ ለእጆችህ ጣቶች
ሰላምታ ይገባል፤ የነገደ ይሁዳና የነገደ
ሌዊ ካህን **ዮሐንስ** ሆይ! በፍዳና በበቀል
ዕለት ነፍሴን የሰለጠነች አድርጋት።

29 **ለገቦከ፡-** በጸሎተ ሐሙስ በእራት
ጊዜ የነበልባል ጐን መጠጊያው ለሆነ
ጐንህ ሰላምታ ይገባል፤ ከተመረጡ
ወገኖች የተመረጥህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ!
ከተመሰገነ አባት አንደበት የወጣች
የአንተ እኅት የሆነች ጥበብ በእኔ ላይ
ትደር፤ እጽፍ ድርብ ትሁን።

30 **ለከርሥከ፡-** መጽሐፍን መብላት በአመረረቻት ፈንታ ለአፍ ለምትጣፍጥ ሆድህ ሰላምታ ይገባል፤ ከብዙዎች የተመረጥህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ከጥምና ከረኀብ ሀገር ወደ ተድላና ወደ ደስታ ሀገር በክንፈ ጸጋህ ውሰደኝ።

31 **ለልብከ፡-** ዕብራውያን ሰቅለው በገደሉት በመምህርህ **በኢየሱስ** መተማመኑን ለአልተወ ልቡናህ ሰላምታ ይገባል፤ በድንግልና እና በንጽሕና የአጌጥህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ነፋስ ከምድር ላይ ትቢያን እንደሚጠርግ በጸሎትህ ኀይል ጠላቶቼን ሁሉ ጥረግልኝ/አጥፋልኝ።

32 **ለኵልያቲከ፡-** የቤት ዕቃዎችን በመብራት እንደሚፈትኑ (እንደሚፈልጉ) **ክርስቶስ** ለፈተናቸው ኵልያቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ ሰርዲስ በምትባል ቦታ መልአክ እያሉ የሚያመሰግኑህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! በሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መልቶ ያለ መንፈስ የአንተ ጸጋ ነውና የተሰጠህ ይህ ጸጋ በእኔ ላይ ይደርብኝ።

33 **ለሕሊናከ፡-** መልካምን እንጂ ክፉን ለማያስብ ሕሊናህ ሰላምታ ይገባል፤ **የሙሴ** ትእዛዝ የሆነ ብሉይንና ሐዲስ ኪዳንን የምትጽፍ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ሀሳቤ ሰማይ እንዲደርስ እዘዘው፤ ያም ባይሆን ጠማማ እንዳይሆን እርዳው።

34 **ለአማውቲከ፡- ክርስቶስ ፈጣሪህ በመስቀል** ላይ ተሰቅሎ ባየኸው ጊዜ በኀዘን ነበልባል ለተቃጠለ አንጀትህ ሰላምታ ይገባል፤ በእውነትና በቅንነት የምታመልከው **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ያንጊዜ ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ ተከተልከው፤ ለወለደችው **ለድንግል እናቱም** መታዘዝን እንቢ ያልህ አይደለም፤ በትሕትና ታዘዝህ እንጂ።

35 **ለንዋየ ውስጥከ፡- እግዚአብሔር** እርሱ የተሰወረውን የሚያውቅ ለመረመረው ውስጣዊ ሰውነትህ ሰላምታ ይገባል፤ **የክርስቶስን ከድንግል** መወለድ የሰበክህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ለእኔ ለባሪያህ የቀናውን መንገድ ምራኝ፤

36 **ለኅንብርትከ፡-** የይቅርታና የርኅራኄ ውኃ ፈጽሞ ለማይለየው የንብቲራ (ማሰሮ) አምሳል ለሆነ ኅንብርትህ ሰላምታ ይገባል፤ እንደቀደመችይቷ ደብተራ ኦሪት የምትጣፍጥ ሽቱ **ዮሐንስ** ሆይ! የጨለማ አበጋዞች ከሆኑ ጠላቶቼ በጸሎትህ ጠብቀኝ፤ በላየ ላይ መከራ እንዳያመጡም በጸሎትህ ሰውረኝ።

37 **ለሐቌከ፡-** በመምህርህ **በኢየሱስ** ቅንዓት (መታጠቂያ) እና በቅድስና መታጠቂያ ለአጌጠ ወገብህ ሰላምታ ይገባል፤ ከሦስቱ ወንጌላውያን አራተኛ የምትሆን **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ከሰማይ እንደወደቁ መላእክት ከሕይወት ጒዳና የራቁ ጠላቶቼን በምልጃህ ጣላቸው።

38 **ለአቍያጺከ፡-** በምሶሶ አምሳል የሥጋህን አዳራሽ ለአነጹና ለአጸኑ ታፋዎችህ ሰላም እላለሁ፤ በማስተዋልና በንጽሕና **የመላእክት** ወዳጅ የሆንህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! በቤትና በመንገድ አውሬ እንዳይነጥቀኝ ለበግህ ጠባቂ ሁነኝ።

39 **ለአብራኪከ፡-** **የክርስቶስን** ወንጌል የሰበክህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ለጕልበቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ የመልኩ ጸዳል እጅግ ለሚያስደንቅ መልአክ በሰገድህ ጊዜ ‹የጌቶችህ ባሪያ ነኝና ለእኔ አትስገድልኝ፤ ስግደትስ **ለአምላክ** ይገባል› በማለት መልአክ ክብርህን ገለጠልህ እኮ።

40 **ለአእጋሪከ፡-** **በክርስቶስ** መነሣት **ጴጥሮስን** እስኪቀድሙት ድረስ ግሥገሣን ለአበዙ እግሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ የእስያና የኤፌሶን መልአክ **ዮሐንስ ሆይ!** በበደል ድንጋይ እግሮቼ ተሰነካክለው ታመዋልና ይድኑ ዘንድ ዳስሳቸው።

41 **ለሰኰናከ፡-** የነጋሲ (የሹም) **የዳዊትን** ቤት ክብር የምትወርስ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ለተረከዝህ ሰላምታ ይገባል፤ አንተ ምድራዊ መልአክ ሰማያዊ ሰው ነህና የዓለም አባት **የአዳም** ጠላት የሆነው ከይሲ እኔን መያዝ

42 **ለመከየድከ፡-** በፍርድ አደባባይ **ከጌታ ኢየሱስ** ጋር በቆመ ጊዜ ዝንባሌ ለሌለው መከየድህ ሰላምታ ይገባል፤ በእሳት ማንደጃ ቤት ለሮምና የተገዛህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! አንተን መጠጊያ አድርጌአለሁና ለዲያብሎስ ከመገዛት ነጻ የወጣሁ አድርገኝ።

43 **ለአፃብዒከ፡-** የኀጢአት ትቢያ ለአልነካቸው ለእግርህ ጣቶች ሰላምታ ይገባል፤ የሚያልፍ የሥጋ ዓለምን ንቀሃልና፤ የነቢያትና የሐዋርያት አንድነት ያሉህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! እግሮቼ ጸንተው እንዲቆሙ አድርግልኝ፤ ወዲያና ወዲህ አትውሰደኝ፤ ወደ ክፉ ቦታም አታውጣኝ።

44 **ለአጽፋረ እግርከ፡-** በመልክ ዳርቻ ለሚቀመጡ ዐሥሩ የእግርህ ጥፍሮች ሰላምታ ይገባል፤ **ቅዱስ ዮሐንስ** በሰማይ ከፍ ያልህ የዓለም አማላጅ ነህ፤ በዕብራውያን አራቱ ከዋክብት ተብለው ከተሰየሙ ደጋግ ሰዎች አንተ ትበልጣለህ።

45 **ለቆምከ፡-** የወንዝ ዳር ዛፍ ለመሰለ ቁመትህ ሰላምታ ይገባል፤ የቁመትህም ጥላ የመጽሐፍ ተራራዎችን የሸፈነ ነው፤ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! አንተን መጠጊያ አድርጌአለሁ፤ ያንጊዜ ሰማያት ቦታ በሚያጡበት ጊዜ ወደቀኝ የምታደርስ የጽድቅ መንገድን ምራኝ።

46 **ለመልክዕከ፡-** የምስጋና እና የዝማሬ መንሻ በማቅረብ ለሚያምር መልክህ ሰላምታ አቀርባለሁ፤ ንጽሕናን እንደግምጃ የለበስህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! የከንፈሬ ፍሬ የሆነ ጸሎቴን ተቀበል፤ ንጹሕ እንደሆነ የዕጣን ሽታም አድርግልኝ።

47 **ለፍልሰትከ፡-** በወንድሞች ዘንድ አይሞትም የሚለው ይህ ነገር ወጣ እንደተባለ ያልሞትህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ለፍልሰትህ ሰላምታ ይገባል፤ በቅድስና እና በንጽሕና ሰውነቶችህ የተጌጡ ናቸው፤ በሚወደድ በገነት ውስጥ ለመመላለስ አሰልጥነኝ/አብቃኝ፤ በዚያ የሚኖሩ የተመረጡ ወገኖች ናቸውና።

48 **ለልብስከ ወለአሚዕኒከ፡-** የመኖርህን ነገር ያስረዳ ዘንድ ለተተወ ለልብስህ ከጫማህ ጋራ ክብር ይገባል፤ **ከመላእክት** ጋር ወዳጅ የሆንህ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ሞልቶ የተትረፈረፈ የፍቅር አንድነትህ ወንዝ በሆዴ ውስጥ የጐደለ አይሁን ይሙላ እንጂ።

49 **ለዘሰአለከ፡-** **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! ‹ለሚለምንህ አትከልክለው› የሚለውን የወንጌል ትእዛዝ ታውቃለህና ከላይ ያለች በረከትህን እፈልጋለሁ፤ ባለፀጋ **ቅዱስ ዮሐንስ** ሆይ! መስጠትህን ችላ አትበል፤ የድኃ ሕይወቱ ልመና ነውና።

50 ኦ ዮሐንስ፥- አባቴ ቅዱስ ዮሐንስ
ሆይ! በንጽሕና ገንዘብህ የእኔን
የኀጢአት ዕዳ ክፈል፤ የሚሸት የእኔን
ሥራም በሽቶ ጸሎትህ መዝምዝ
(ለውጥ)፤ መሥዋዕት የምታሳርግ ክቡር
ዮሐንስ ሆይ! እኔን ለመባረክ
ከወንድሞችህ ሐዋርያት ጋራ ና!
በልቡናየ ውስጥ ፍቅርህ ሞልቷልና።

## ሰላምታ

1 ሰላም ለከ፥- የኢየሱስ ክርስቶስ
ወዳጅ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ሆይ!
ሰላምታ ይገባሃል፤ አቡቀለምሲስ
የተባልህ ክቡር ዮሐንስ ሆይ! ሰላምታ
ይገባሃል።

2 ሰላም ለከ፥- የሐዲስ ሥርዐት
ሐዋርያ ዮሐንስ ሆይ! በቤተ ምንዳድ
ለደረሰብህ መከራ ሰላምታ ይገባሃል፤
በትዕግሥትህ የሮምናን ቍጣ ችለህ
የሞተውንም ልጅ የአስነሣህ ቅዱስ
ዮሐንስ ሆይ! ሰላምታ ይገባሃል።

3 ሰላም ለከ፡- መከራን የምትታገሥ
ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! እንደ አንተ ያለ
በምድር ላይ ማነው! ክብርን የተሞላህ
ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! ሰላም ለአንተ
ይሁን እያልሁ በምስጋና እና
በዕንቢልታ የቤተ ክርስትያን የጉባኤዋ
መሪ እነሆ አደንቅሃለሁ፤ በምስጋና እና
በማኅሌት የመላእክት ወዳጅ የሆንህ
እውነተኛ ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! ሰላም
ለአንተ ይሁን፤ ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ!
ለሚልህ የመልክህ ደምግባት ምን
ያምር! የስምህስ አጠራር ምን
ይጣፍጥ!

4 ሰላም ለከ፡- አራተኛውን ወንጌል
የጻፍህ ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! ሰላምታ
ይገባሃል፤ ኮል የተባለ የምስጋናህ መዓዛ
በሰው ሁሉ አፍንጫ በጐ በጐ ሸተተ፤
ንስር የተሰኘህ ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ!
ልዑል ከሆነ ከሰማይ ተዋሕዶ ያ ቃል
ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ እያልህ በርረህ
ና!

5 አቅረብኩ ለከ፡- የእግዚአብሔር
ወልድ እናቱ የድንግል ማርያም
ባለሟል ቅዱስ ዮሐንስ ሆይ! በዘጠኙ
ሊቃናት አርአያ ሰላምታ
አቀርብልሃለሁ፤ የከንቱ ጸጋ ዋጋ
ያልተከፈለበትን ክብር አድለኝ/ስጠኝ።

6 አቤቱ የቅዱስ ዮሐንስ ወልደ
ነጐድጓድ አምላክ ሆይ! ከክፉ ነገር
ጠብቀኝ፤ ከነፍስ ከሥጋ መከራ
አድነኝ፤ ሰውረኝ፤ በሰው ዘንድ
መወደድን ስጠኝ፤ ቤቴን ንብረቴን
የቀና አድርግልኝ ለዘለዓለሙ አሜን።

7 አባታችን ሆይ...